# ትንሹ ሰይጣን

አጭር ልብወለድ

## ከደረጀ በቀለ

በአውራ ጎዳናው ላይ ከሚተራመሰው ህዝብ ፊንጠር ብዬ ወጣሁና ብቻዬን ቆምኩ። አለባበሴን ከታች ወደ ላይ ቃኘሁና ህፍረት ተሰማኝ። ያደፈ ሸራ ጫማ፤ ጉልበቱ ላይ መንተብ የጀመረ ካኪ ሱሪ፤ የተጨማደደ እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ። “ወይኔ ቸንቶ!” ጸጉሬን በቁጭት ነጨሁ።

በኪሴ ያለውን ገንዘብ አወጣሁና ቆጠርኩ። ሀያ አንድ ብር። ከአምስት ቀን በፊት ከወህኒ ቤት ስወጣ መቶ ሀምሳ ብር ነበረኝ። አዲስ አበባ ጨሳለች። ከአሥራ አራት ዓመት በፊት የማውቃትን አዲስ አበባ እንዳስቀመጥኳት አላገኘኋትም። የሰው ብዛት አስደነገጠኝ። የሰው ፍጥረት ከዝናቡ ጋር ከሰማይ እንደሚዘንብ። ከየድንጋዩ ሥር እንደ ቁጫጭ ተፈልፍሎ እንደሚያድር ሁሉ ከተማዋን በየአቅጣጫው አጥለቅልቋታል።

ደግሞ ሁሉም በጥድፊያ ነው የሚጓዙት። ትከሻ ለትከሻ እየተላተሙ፤ ቂጥ ለቂጥ እየተጋፉ። ‘ይቅርታ’ አይባባሉም። ለትራፊክ መብራት አይቆሙም። ገልመጥ ብለው ወደ ኋላቸው አያዩም። ተማክረው እንዳበዱ አይነት ሁሉም በመሄድ ቀልባቸው ጠፍቷል። ከመሄድ የሚገኝ ጥቅም እንዳለ ብዬ እኔም ሦስት ቀን ሙሉ በከተማዋ አስፋልቶች ላይ ተንቀዋለልኩ። ጠብ ያለልኝ ነገር የለም። ዘግይቼ አንድ ነገር ተገነዘብኩ። ለካስ ከተሜውን እንዲህ የሚያከንፈው፤ እሾህም ጥፍሩን አሹሎ ከጀርባው የሚያሳድደው “ኑሮ” የሚባል ጠላቱ ነው።

ይሄው ዛሬ እኔንም ጥፍሩን አሹሎ ማጅራቴን ከማነቁ በፊት ልሸሽ ነው። አንድ ነገር ያስጨንቀኛል። ጥርሴን ነቅዬ ያደግኩባት ከተማ ትዝታ አይደለም። የአስፋልቱና የህንፃዎቹ፤ ወይም የህዝቡ ፍቅር አይደለም። ጭንቀቴ አዲስ አበባን ለቅቄ የት እንደምሄድ ብቻ ነው።

ይች አሲዳም ከተማ ጥርስ አውጥታ ሳትበላኝ ማምለጥ አለብኝ። ያውም ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ፍጥነት። መንገደኛውን እየገፈታተርኩ፤ እንደጥይት ከሚከንፉ ታክሲዎች ጋር እየተጋፋሁ፤ ዛሬም እንደ ትላንቱ ውሎዬ ወደ አውቶቡስ ተራው ተጣደፍኩ።

በአውቶቡስ መናኸሪያው አጥር ላይ አንገቴን ሰገግ አድርጌ ወደ ውስጥ ተመለከትኩ። ተሣፋሪ የሚጭኑና የሚያወርዱ አውቶቡሶች ቅጥር ግቢውን አጨናንቀውታል። በሸሚዝ ኪሴ ውስጥ ያስቀመጥኳትን ሀያ አንድ ብር አውጥቼ እጥፍጥፍ አደረኩና በሱሪዬ የምስጢር ኪስ ውስጥ ቀረቀርኳት። የቅጥር ግቢውን በር አልፌ ከመግባቴ ቆም አልኩና አዲስ አበባን በሦስት አቅጣጫ ‘ለመጨረሻ ጊዜ’ ብዬ ተመለከትኳት። እንግዲህ በዚች ከተማ ውስጥ ቀረኝ የምለው ምንድን ነው?! ራሴን ለአፍታ ጠየኩት።

ወዲያው በአሥራ አራት ዓመት የውህኒ ቤት ቆይታዬ ውስጥ አልፎ አልፎ ህሊናዬን እየሞገተ ሲያስጨንቀኝ የነበረ አንድ ጥያቄ ድንገት በህሊናዬ ደወለና በቆምኩበት አደነዘዘኝ።

“አሥራ አራት ዓመት ያለፈው.....የተረሳና ያረጀ ታሪክ እንደተዳፈነ እሳት ጊዜ ጠብቆ የህይወት እሥረኛ ሊያደርገኝ ነው?!” ራሴን ጠየኩ። እንደዚያ ከሆነማ ስንቱን ዓመት በልቡናዬ አዝዬ ስሰቃይበት ለኖርኩት ጥያቄ መልስ ለማግኘት አዲስ አበባ መቆየት ሊኖርብኝ ነው። ግን ምን ያህል ጊዜ?! ሀያ አንድ ቀን.....ሀያ አንድ ወር፤ ወይስ ሀያ አንድ ዓመት?! በኪሴ ውስጥ ያለኝ የመጨረሻ ንብረት ሀያ አንድ ብር ብቻ መሁኑ ሲታሰበኝ የሚታገለኝን ጭንቀት ለማባረር ራሴን ደጋግሜ ወዘወዝኩና የቅጥር ግቢውን በር አልፌ ገባሁ።

በእርጋታ እየተራመድኩ ሄጄ የግንቡን አጥር ተደግፌ ቆምኩ። ዛሬም ያው ትላንት እንዳየሁት ትርምሱና ጫጫታው ራስ ያዞራል። ሲጋራ አውጥቼ ለኮስኩና ማሰብ ጀመርኩ። አሁን በአንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ። እሄዳለሁ። ወዴት?! የሚለውን ጥያቄ ግን መመለስ ነበረብኝ። አዲስ አበባ አምስት በሮች አሏት። በአንደኛው መሹለክ የግድ ነው። ግን በየትኛው?!

እያንዳንዱ በር የት እንደሚያደርስ፣ መድረሻውስ ላይ ምን ሊያጋጥመኝ እንደሚችል ገመትኩ። ከዚህኛው ያኛው ይሻላል ብዬ ሀሳቤን መቁረጥ ግን አልሆነልኝም። በሀሳብ ሙብከንከኑ ሲሰለቸኝ “ዕድል ባሻት አቅጣጫ ወስዳ ከፈለገችበት ትጣለኝ!” አልኩና ካሸለብኩበት እንቅልፍ ነቃሁ።

በጄ ላይ የምትጨሰው ሲጋራ ተጋምሳለች። ልምጥጥ አድርጌ ሳብኳትና ጭሱን በአፍንጫዬ እያትጎለጎልኩ ካቀረቀርኩበት ቀና አልኩ። አንድ ልጅ ከትርምሱ መሀል እይተሹለከለከ ወትቶ ፈገግታ እያሳየ ቀረበኝ። ትላንትናም እዚሁ ግቢ ውስጥ እንደ ተልከስካሽ ውሻ ከወዲያ ወዲህ ሲንቀዠቀዥ አይቸዋለሁ። ሣንቲም ሊለምነኝ መሰለኝና ውስጤ እየሳቀ ግንባሬን አጨፈገግኩበት። ልጁ ግን በቀኝ እጁ መሀል የያዛትን የሲጋራ ቁራጭ እያሳየኝ “ጋሼ እሳቷን” አለኝና ከወገቡ ጎንበስ አለ።

ሁኔታው ሁሉ የሚገርም ፍጥረት ነው። በውርጭ የተጠበሰ ጠይም ፊቱ አመድ መስሏል። በጫት የተወጠረ የግራ ጉንጩ የውርጩን ንቃቃት አጉልቶ ወለል አድርጎታል። ያለመጠን ባደገው ዞማ ፀጉሩ ላይ የተዘራው የቅጫም ዘር በርቀት ፀጉሩን ሸበቶ አስመስሎታል። እጅጌ የሌላት ቢጫ ሹራቡ አዳፋና አጥንታም ደረቱን አጋልጣዋለች። ቡናማ ቀለም ያላት ቦላሌ ሱሪው ብን ብላ በላዩ ላይ ተበጣጥሳለች። ባዶ እግሩ ሬንጅ እንደጠገበ አዲስ አስፋልት ጽልመት ለብሷል።

ከላይ እስከታች እየቃኘሁ ኡኔታውን ሳጠና “እሳቱን ግፋ!” አለኝ በቁጣ። ፈገግታው ከፊቱ ላይ ተገፎ ጠፍቷል። “አይ አዲስ አበባ....ለዚህ ገና ወተት ላልጠገበ ልጅ ሲጋራና ጫት?!” የአራዳን

አድባር ወቀስኳት። ይሁን እንጂ፤ በዚያ ብቸኝነት አጥንት ሰርስሮ እንደሚገባ ብርድ ባቆራመደኝ ክፉ ሰዓት አፍ የሚያካፍት የሰው ፍጡር አጠገቤ በማግኘቴ ደስ አለኝ። "ስምህ ማነው?!" አልኩት የውሸት ፈገግታ ለማሳየት እየሞከርኩ።

ገና በልጅነቱ ቀልተው ደም በለበሱ ጎላ ጎላ ያሉ ዐይኖቹ ከላይ ወደታች ከገላመጠኝ በኋላ "ምን ያደርግልሃል?!" አለኝ፤ ግንባሩን ቁጥር አድርጎ። አንድ ሲጋራ ከኪሴ አወጣሁና እጄን ዘረጋሁለት። የተጨማደደ ገጽታው በአፍታ ፈክቶ ፈገግታ አሳየኝ። ፈጥኖ በእጁ የያዛትን የሲጋራ ቁራጭ ከጆሮ ግንዱ ከተተና የዘረጋሁለትን ሲጋራ ተቀበለኝ።

"ስምህ ማነው?!" እንደገና ጠየኩት።

"ቡቾ"

"ቡቾ?!" በመገረም አስተዋለኝ።

"ቡቾ የውሻ ስም እንጂ እንዴት " የጀመርኩትን ሳልጨርስ ከትከት ብሎ ሳቀ። ሲስቅ ጥርሶቹ ወለል ብለው ታዩኝ። ውልግድግድ ያሉና በሲጋራ ጢስ የጠቆሩ ናቸው።

"ምን አሳቀህ?!"

"አንተ ነህ...የውሻና የሰው ስም እንኳን አትለይም?! ቡቾ ማለት አታውቅም?! ቡቾ ማለት እኮ..." የጀመረውን ሳይጨርስ ከሱሪው ኪስ ጥቂት የጫት ቀንበጥ አውጥቶ ወደ ተወጠረው ጉንጩ ከተተና ማኘኩን ቀጠለ።

"ቡቾ ማለት ምንድንነው?!" የጀመረውን እንዲጨርስ መንገድ ከፈትኩ።

ትከሻውን ሰበቀና "እንጃ....ረሳሁት" አለኝ። ለአፍታ ያህል በነኛው የቀሉ ዐይኖቹ ደግሞ ከላይ እስከታች ቃኘኝና "ችስታ ነሽ .... አይደል ?!" እዚህ ቆመሽ ከምትፈላሰፊ ለምን ዞር ዞር ብለሽ አትሸቅይም?!" ሲል ጠየቀኝ።

በዚህ የድፍረት ንግግሩ ድንገት ብልጭ አለብኝ። በጥፊ ልለጋው እጄን ካነሳሁ በኋላ መልሼ ተውኩት። ጉሮሮዬን ያነቀኝን እልህ እንደምንም ውጬ ራሴን ካረጋጋሁ በኋላ ነበር ልጁ የተናገረው እውነት መሆኑን የታዘብኩት። አሁንስ ቢሆን እንደ ቡቾ ቋንቋ ችስታ፣ እንደ ሌላውም መናጢ እንጂ ሌላ ምንድን ነኝ?! የድሮውማ ድሮ ቀረ።

"ችስታ መሆኔን በምን አወቅክ?!" ውስጤ እየጨሰ የውሸት ፈገግታ አሳየሁት። በሌባ ጣቱ ወደ እግሬ እያመለከተ "ያረጀ ሸራ ነዋ የገደገድሽው" አለና በሽሙጥ አሽካካብኝ። ጎንበስ ብዬ የገዛ ጫማዬን እንደ አዲስ ተመለከትኩት። ወይኔ ቸንቶ!

"ስንት ዓመትህ ነው?!"

"ምን አገባህ?!"

"ምንም" ንዴቴ ቀረና በህፍረት ተሸማቀኩ። በጄ የያዝኳትን የሲጋራ እላቂ ተቀበለና ሁለት ሦስት ጊዜ ከሳበላት በኋላ የሰጠሁትን ሲጋራ አቀጣጠለበት። ስስታምነቱ ገረመኝ። ከፊት ለፊቴ ካለ ድንጋይ ላይ ቁጢጥ ብሎ ትቀመጠና ሲጋራውን እየሳበ ሲመለከተኝ ቆየ። "ገምት እስኪ ስንት ዓመት የሚሆነኝ ይመስልሃል?!..."

"አስር" አልኩት፤ አፌ እንዳመጣልን።

"ሦስት ዓመት ደምርበት" አለኝ እየተኩራራ።

"የአሥራ ሦስት ዓመት ልጅ?!" አልኩ፤ የድሜውን ማነስ ከግንባሩ፣ ከአነጋገሩና ከድርጊቶቹ ሁሉ ጋር እያነፃፀርኩ።

ከተቀመጠበት ድንጋይ ላይ ሲነሳ ሊሄድ መሰለኝና "ወዴት ነህ?!" አልኩት።

ገልመጥ ብሎ አይቶኝ መልስ ሳይሰጠኝ ወደግንቡ ጥግ ሄደና ፊኛውን አስተንፍሶ ተመለሰ። ከነበረበት ድንጋይ ላይ ተመልሶ ሲቀመጥ ፊቱ ላ የስቃይና የጭንቀት ስሜት ያየኡ መሰለኝ። ለምን እንደሆነ ባላውቀውም ሁኔታው፣ አነጋገሩ፣ አስተያየቱ ሁሉ ስቦኛል። ከዚህም በላይ ደግሞ የልጁን ገጽታ ለረዥም ጊዜ የማውቅውን ዓይነት ገጽታ ሆኖ ተሰምቶኛል።

"ምነው ቡቾ.... አመመምህ እንዴ?!" ስል ጠየቅኩት፤ በገጹ ላይ የማየው ስቃይ ስለሰቀቀኝ። በሚያጨሰው ሲጋራ ከሰራቸው ቀለበቶች ላይ ዐይኖቹን እንደተከለ፦

"እንደገና ጎኖሪያ ጨመደደኝ ማለት ነው?!" አለና ለራሱ ያህል አጉተመተመ። ጆሮዎቼ የሚሰሙትን ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ ባለሁበት ደንዝዤ ቀረሁ። "ያች የጠነዛች ተላ ነጋዴ አሮጊት ሠራችልኝ....ትፈነግለኛለች ማለት እኮ ነው....ለሁለት ብር ብላ....ከማጅራት መችው ጋር ....ወይኔ ቡችዬ እንደገና ደግሞ ጎኖ....እናቷን !" ምራቁን ጢቅ ብሎ መሬት ላይ ተፋ።

ፈራሁት። ከፊት ለፊቴ የተቀመጠው ሰው ሳይሆን ትንሽ ሰይጣን መሰለኝ። አፌን ሰብስቤ ብዙ ከቆየሁ በኋላ፣ "ሀኪም ቤት መሄድ አለብህ ቡቾ" አልኩት፣ እያስተዛዘንኩ።

ፈገግ ብሎ እንዚያን የዛጉ ጥርሶቹን አሳየኝና "እሱን ለኔ አትምከረኝ....በአንድ ብር አምፒሲሊን ድራሹ ይጠፋል....አሮጊቷን ግን አንድ ቀን እግድላታለሁ....በኔ ላይ ደርባ ከማጅራት መቺው ጋር .....ለሁለት ብር ብላ እኮ ነው.... "በቁጭት ተንጨረጨረ።

"እናትና አባት አሉህ?!"

"ለምንድን ነው ምርቃናዬን የምትደብረው?! ደግሞስ ምን አገባህ?!" ጎረጥ ዐይኖቹን አፈጠጠብኝ።

"ምንም"

"ግን አንተ እዚህ ምንድን ነው የምትሠራው?!" በጥርጣሬ ተመለከተኝ።

"ምንም"

"ታዲያ ዞር ዞር ብለህ ለምን አትሸቅልም?!"

"ምንድን ነው የምሸቅለው?!" በመገረም ሲመለከተኝ ቆየና፣ "ጥፍራም ነህ እንዴ?! ሲያዩህ ግን ችስታ እንጂ ጨለሌ አትመስልም.... እና ሸቀላ አታውቅም?!"

"አላውቅም"

"እንግዲያውስ ጥፍራም ነሽ...አየሽ?! ሸቀላ ማለት ገንዘብ የሚያስገኝ ማንኛውም ዓይነት ሥራ ነው። ተሣፋሪዎች ከመኪና ሲወርዱ ሻንጣቸውን አንከብክበሽ ታክሲ ታሳፍሪያልሽ ........ መኪና ትጠብቂያለሽ ..... ለተሣፋሪ የትኬት ወረፋ ትይዣለሽ ...አይዞሽ ሸቀላ ማለት ምን እንደሆነ ወደፊት ትረጂዋለሽ።" አለኝ፤ ዐይኖቹን በሚተራመሰው ህዝብ መሀል እያንቀዋለለ።

እንደበፊቱ አልተናደድኩም። በዕድሜ ሦስት ጊዜ እጥፍ የምበልጠው ህፃን "አንቺ" እያለ ሲያንኳስሰኝ የቀድሞ ክብሬንና ደረጃዬን እያሰብኩ ከማዘን በቀር በቡቾ ላይ አልፈረድኩም። የህይወት ፍርጃ እንጂ ይሄንማ ምን ይሉታል?!

"ስንተኛ ክፍል ደርሰአል?!"

"አልተማርኩም"

"ለምን አልተማርክም?!"

"የሚያስተምረኝ የለም!"

"አባትና እናት የለህም?!"

"አንቺ ሰውዬ ምነው ጥያቄ አበዛሽ? ኡጄ (ፖሊስ) ነሽ እንዴ?" በጥርጣሬ ሸቅብ እያየኝ እጁን ብብቱ ሥር ሰደደና ማከክ ጀመረ።

"ጨዋታህ ደስ ስላለኝ እኮ ነው ቡቾ" አልኩት አሁንም የውሸት ሳቅ እየሳቅኩ።

"ያስከፍልሻላ!" አለኝ እየፈገገ። በእውነትም ስሜትን የሚስብና ቀልብ የሚሰርቅ አንድ ዓይነት ምትሃት አለው። በኪሴ የቀረኝን የመጨረሻ ሲጋራ

አወጣሁና ከክብሪት ጋር ወረወርኩለት። የወረወርኩለትን ሲጋራ ቀልቦ በጆሮ ግንዱ ላይ ወሸቀና ከጆሮው ጋር ያጣበቃትን እላቂ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሳት። ክብሪቴን ግን ሱሪ ኪሱ ውስጥ ከተተው። ዝም አልኩ።
“አባትና እናት የሉህም ወይ ነው ያልከኝ?!” አለኝ። ሲጋራውን ደጋግሞ ሳባት።

“ታዲያ ለምን አላስተማሩህም?!” ፍዝዝ እንዳለ በእግሩ አውራ ጣት መሬቱን ሲጭር ቆየና ...”እናቴ መጠጥ ቤት ነው የምትሠራው ... አባቴ ደግሞ ሰው ገድሎ ታስሯል” አለኝ።
“እናትህ ማን ትባላለች?!” እየተጣደፍኩ ጠየቅኩት።

“አቦ .... ተወና .... በአንድ ሲጋራ ምን ታናዝዘኛለህ?!” አለና ዐዮቹን ከትርምሱ መህል አሰረጋቸው። ከመንጋው ገንጥለው እንደለዩት ፈጋ መልሶ ወደ ትርምሱ ሊቀላቀል ሲያኮበኩብ አስተዋልኩት።

“ትንሽ እንድንጫወት ብዬ እኮ ነው .... ደኦ ለምሳህ ሣንቲም እሰጥሃለሁ!” አልኩት፤ ለማግባባት። እውነቴን ይሁን ውሸቴን አላውቅኩትም። ብቻ “አባቴ ታስሯል” ሲለኝ አንዳች የበረዶ ማዕበል በሆዴ ውስጥ መገልበጥ ጀምሯል።

“እናትህ ማን ትባላለች?!” ጥያቄዬን ደገምኩለት።
“ሰላማዊት ትባላለች”
“ምን ትሠራለች?!”
“ሸሌ ነች። እዚ ንጋት ሆቴል ውስጥ መጠጥ ታቀርባለች። አንዳንድ ቀን ሸቀላ ሲጠፋ .... ሲርበኝ .... እሷ ጋ እሄድና .... ሳቢ (ገንዘብ) ትበጥስልኛለች። ውው ደግ ነች። ባየችን ቁጥር ታለቅሳለች። አብረን እንዳንኖር ግን ቤት የላትም። እሷም ለራሷ በአንድ ክፍል ውስጥ ከመዓት ሸሌዎች ጋር ነው የምታድረው” አለኝ ጫቱን ቶሎ ቶሎ እያኘከ።

“ሰላማዊት ማ?!” አልኩት አንደበቴ ተሳስሮ።
“ሰላማዊት እዝራ!”
“የአባትህ ስም ማነው?!” የገዛ ስሜን ጠራልኝ! በውነትም ህይወት የብዙ የማይታመኑ አጋጣሚዎች መድረክ ናት፤ አሥራ አራት ዓመት ሙሉ በህሊናዬ ተሸንቅሮ ሲሞግተኝ ለኖረ ጥያቄ መልስ አገኘሁ።

“ታውቃታለህ እንዴ?!” ጠየቀኝ ቡቹ።

“አላውቃትም!” አልኩት ተቆጥቼ፤ ነብር ሆኜ። በህይወቴ ይህንን ስም ለስንተኛ ጊዜ ካድኩት? ለመጨረሻ ጊዜ ያየኋት መቼ ነበር?! ከአሥራ አራት ዓመት በፊት በአንድ ዝናባማ ምሽት ነው። ጥንብዝ ብዬ ሰክሬያለሁ። የቤቴ በር ሲደበደብ ሰዐቴን ተመለከትኩ። ከምሽቱ አምስት ሰዐት አሳየኝ። እየተወላገድኩ ሄጄ ከፈትኩት። ሰላማዊት ነበረች። ከፀጉሯ ላይ እየተንከባለለ ፊቷን የሚያጥበውን የዝናብ ውሃ በእጇ እየጠረገች ቆማለች። ግንባሯ ተቋጥሯል። እንባዋ በሁለቱም ግንጮቿ ላይ ኩልል እያለ ይፈሳል።

“ለምን መጣሽ?!” እየተንተባተብኩ አፈጠጥኩባት። ገፍተር አድርጋኝ ወደ ውስጥ ጋባችና ቆመች። ጎላ ጎላ ያሉ ዐይኖቿ ዙሪያውን ደም አርግዘዋል። በውሀ የራሰ ረዥም ፀጉሯ በየአቅጣጫው ተበታትኖ ፊቷን አልብሶታል። በቁጭት ከንፈሯን እየነከሰች አፈጠጠችብኝ። ከሞት ጋር ፊት ለፊት የተፋጠጥኩ መሰለኝናፈራሁ። “በሆዴ የተሸከምኩትን ጽንስ ምን እንደማደርገው ብቻ መልስ ስጠኝ!” ድምጿ እየተንቀጠቀጠ ጮኸች።

“ስለምታወሪለት ጽንስ የማውቀው ነገር የለም ..... አንችንም አላውቅሽም!”

“አባት የሌለው ልጅ በሆዴ ለመሸከም አለፈልግም። ትሰማኛለህ?! ሴት ያሳደገው ልጅ የሚሰኝ ምስኪን ፍጥረት ሆዴ ሊሸከም አይችልም!” መላ አካሏ መንቀጥቀጥ ጀመረ። ዝም አልኩ።

“ነገ የሀገርና የወገን ሸክም የሚሆን ..... ከርሞ በወኅኖቹ አንገት ላይ ስለት የሚስል፣ ሰብሳቢ ያጣ እኩይ ፍጥረት መሀጸኔን አልፎ እንዲወጣ አልፈቅድም!” አሁንም ዝም አልኳት።

“የገዛ ስሟን ጠርታ የአብቷን የማትደግም ..... የዲቃላ ልጅ በመባሏ በጓደኞቿ ፊት የምታፍር፣ ስም የለሽ ፍጥረት አምጬ አልወልድም!” አለችና ጥፍሯን አሹላ እንደ ነብር ተወረወረችብኝ። ዞር ብዬ አሳለፍኳት። ከግድግዳው ጋር ተላተመች። እጅዋን ጠምዝዤ ከክፍሉ ውስጥ አስወጣሁና በሩን ዘጋሁ። “አስወጣዋለሁ!” ብላ ስትጮህ ለመጨረሻ ጊዜ ድምጿን ሰማሁ። ፈጥኜ መብራቴን አጠፋሁና ጥቅልል ብዬ ተኛሁ።

ከዚያ በኋላ አላየኋትም። ልጁን ታስወጣው፣ ከነህይወቱ ትውልደው አላውቅም። በዚያው ዓመት የአለቃዬን ነፍስ አጥፍቼ ተፈርዶብኝ ወህኒ ገባሁ።

ቡቹ ያለቀች ሲጋራውን በጥፍሩ ይዞ ልምጥጥ አድርጎ ሳበና ወረወራት። ከንፈሩ ደርቆ ኩበት መስሏል። ይህ ከፊቴ የተቀመጠው ትንሽ ሰይጣን የስጋዬ ቁራጭ፤ የደሜ ቅጅ፤ የገዛ ልጄ መሆኑን ሳስብ በቆምኩበት ተንቀጠቀጥኩ። ነፍሴ በውስጤ እሪ ብላ ጮኸች። እንባዬ ጉንጬን ሲያረጥበኝ ታወቀኝ። እንዳያየኝ ፊቴን ጠምዝዤ ጠርግኩት። እቅፍ አድርጌ ልስመው አሰብኩ። ድፍረት ግን አልነበረኝም። ቀድሞ ነገር ይኼንን ሰይጣን አብትህ ነኝ ለማለት ምን ሙብት አለኝ? ሽሽ ሽሽ ... አምልጥ አምልጥ ..... ጥፋ ጥፋ” የሚል ስሜት ከውስጥ ይታገለኝ ጀመር። ቀና ብዬ ወደቲኬት መቁረጫው ቢሮ ተመለከትኩ። ግፊያውና ትርምሱ ልክ የለውም።

“ቡቹ ቲኬት ልታስቆርጥልኝ ትችላለህ?!”
“ሳቢ ከበጠስሽ ምን ቸገረኝ ... ወዴት ነሽ?!”
“ወደ አሰላ” አፌ ያመጣልኝን የከተማ ስም ጠራሁለት። በሚስጥር ኪሴ ካስቀመጥኩት ሀያ አንድ ብር ሀያውን ሰጠሁትና አንዷን ወደ ደረት ኪሴ ሸጎጥኩ። እየሳቀ ተቀበለኝ። “ምን ያስቅሀል?!”
“ጥፍራም ነሽ .... ብር እንዴት ምስጢር ኪስ ውስጥ ይቀመጣል?!”
“ይልቅ ፍጠን ቡቹ!”

ብር ብሎ ሄዶ ትርምሱ ውስጥ ተቀላቀለ። ያለ መሰልቸት አንድ ሰዐት ያህል ጠበቅኩት። አልተመለሰም። ቡቹን የበላ ጅብ እንኳን ሊጮህ አላስነጠሰም። መገተሩ ቢሰለቸኝ ዞር ዞር ብዬ ፈለግኩት። አላገኘሁትም። ቢቸግረኝ አንዱን ሸቃይ ጠጋ አልኩና “እባክህን ወንድም ቡቹን አይተሃል?!” ስል ጠየቅኩት። ቀና ብሎ ለረዥም ጊዜ ሲያየኝ ከቆየ በኋል፤

“አላየሁትም .... ገንዘብ ሰተኸው እንዴ?!” ሲል ጠየቀኝ።
“አዎን ... ቲኬት እንዲያስቆርጥልኝ ... ሀያ ብር ... “ ሰውዬው በሳቅ ይንከተከት ጀመር። በአፍታ ብዙ ሰዎች ከበቡን።

“ቡችዬ ሰይጣኗ .... የሰውዬውን ሀያ ብር አስነጠሰችው!” በአዋጅ ነጋሪ ድምጽ ጮኸ። የከበቡን ሰዎች ሁሉ በአንድነት ሳቁ።

“ቡችዬ የዛሬ ጨብሲ ሞተላት ማለት ነው” ሌላው ቀጠለ።

“ለተላ ነጋዴዋ አሮጊት ጥበብ ያሰፋላታል።”
“ቡችዬ አምፒሲሊን መግዣ ቀናት ....”
“ጠዋት ፖሊሶች ይፈልጓት ነበር .... ምን እንዳደረገች እኔ እንጃ ....
“ቡችዬ ሰይጣኗ! ቡችዬ አንበሳዋ! ቡችዬ ቁጭ ይበሉዋ! ....

ጫጫታው ራሴን አዞረው። ከግርግሩ መሀል ቀስ ብዬ ወጣሁን ወደቅጥር ግቢው የመውጫ በር አመራሁ። በኪሴ የቀረችው አንድ ብር መኖሯን አረጋገጥኩና ተጽናናሁ። ሁለት እጆቼን በሱሪዬ ኪስ ውስጥ ከትቼ አፏጨሁ። ግቢውን ለቅቄ ስወጣ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም። እግሮቼ ብቻ ያለ ዓላማ ይራመዳሉ። አዕምሮዬ ማሰብ ያቆመ ይመስለኛል። ዐይኖቼ ከጫፍ እጫፍ እየሮጡ “ንጋት ሆቴል” የሚል ጽሁፍ ያማትራሉ።